# በኢትዮጵያ የዋሀቢ አክራሪ እሥልምና አደጋ

አብዱል ከሪም

እሥልምና ወደ ኢትዮጵያ የገባው በነቢዮ መሀመድ ዘመን ነው፡፡ ከዚያን ዘመን ጀምሮ በኢትዮጵያ ወስጥ ቀድሞ ከነበረው የኦርቶዶክስ እምነት በመቀጠል አንጋፋ ኃይማኖት ሆኖ ኖሯል፡፡

ኢሥላም ትርጉሙ ራሱ ሠላም ማለት መሆኑን የኃይማኖቱ አባቶች ይናገራሉ፡፡ ኢትዮጵያን ከሌላው ዓለም ልዩ አድርጎት የኖረው አንዱ ነጥብ ኃይማኖታዊ መቻቻልና መከባበር የሰፈነባትና ለሌሎች ምሣሌ በመሆኗ ነው፡፡

ከሁሉም የኢትዮጵያ የቀድሞ መንግሥታት በተለይም በአሁኑ ወቅት በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት የኃይማኖት ነፃነት በሕገ መንግሥቱ እንዲከበር በማድረግ፡ በኃይማኖታዊ ጉዳይም ጣልቃ የማይገባ በመሆኑ፡ ዜጎች በነፃነት የፈለጉትንና የሚጠቅን የእምነት ነፃነት የመከተል መብታቸው በሕግ የተረጋገጠ ነው፡

ከቅርብ ዓመታት ወዲህና በቅርቡ ከእሥልምና ኃይማኖት ጋር የተያያዘ አዲስ ክስተት ኢትዮጵያ እያስተናገደች ነው፡፡ በኢትዮጵያ ወስጥ ጥንትም የነበሩትና ያሉት የእሥልምና እምነት አራማጅ አባቶች ይከተሉት የነበረወና ዛሬም ያለው የሱፊ እሥልምናን ነው፡፡

ሠላማዊና ተቻችሎ በመኖር የዘለቀ ነው፡፡ መነሻወን ከሣወዲ ዐረቢያ ያደረገው የዋሀቢ አክራሪ እሥልምና እምነትን ወደ ኢትዮጵያ አሰርጎ ለማስገባት፡ ለበርካታ ዓመታት ወስጥ ለወስጥ ብዙ ሲሰራበት ከቆየ በኋላ በኢትዮጵያ ለረዥም ዘመን የኖረወን የሱፊ እሥልምና ለማጥፋት የዋሀቢ እምነትን ለማስፈን እንቅስቃሴዎቹ ጎልተው ታይተዋል፡፡ ከፍተኛ ተቃወሞም ገጥሞታል፡፡

በኢትዮጵያ የዋሀቢ አክራሪ እሥልምና ኃይማኖትን ለማስፋፋት ቁልፍ ሚና የተጫወቱት በሣወዲ ዐረቢያ ለሥራና ለትምህርት የሄዱና የተመለሱ ኢትዮጵያወያን ናቸው፡፡
እነዚህን በማጠናከርና በማገዝ ረገድ የተሰለፉት ደግሞ ኢትዮጵያ ወስጥ ፈቃድ አግኝተው በመግባት የሚንቀሳቀሱ የሣወዲ ዐረቢያ፣ የኩዌትና የኳታር መንግሥታዊ ያልሆኑ እሥላማዊ ድርጅቶች መሆናቸወን ዊክሊክስ ከኢትዮጵያ የአሜሪካን ኤምባሴ ወደ ዋሽንግተን ያስተላለፈወን ከፍተኛ ምስጢራዊ ዶክመንት ይፋ አድርጎታል፡፡

ዋሀቢ አክራሪ እሥልምና በተለይ ዓላማ አድርጎ የተንቀሳቀሰው በአማራውና በኦሮሚያ ክልሎች ነው፡፡ ነባሩን የሱፊ እሥላም እምነት ለማጥፋት ለዓመታት ሰርቷል፡፡

በዚሁ መረጃ መሠረት ባለፉት 10 ዓመታት ኩዋይቲ ተብሎ በሚጠራ የኩዌት መንግሥታዊ ያልሆነ እስላሚዊ የበጎ አድርጎት ድርጅት አማካይነት ከደሴ አካባቢ በመጀመር ወደ ሰሜን ትግራይ ድረስ እያንዳንዳቸው 540 ሺህ ብር (30 ሺህ 000 የአሜሪካን ዶላር) የሚያወጡ ከ150 በላይ መስጊዶችን አሰርቷል፡፡

በቀላሉ ሊለዩ የሚችሉና አረንጓዴ ባለአንድ ፎቅና ሚናሬት ያላቸው ናቸው፡፡ ከአካባቢውም ጋር ሲታዩ ይስባሉ፡፡ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች በባህላዊ መልኩ ከሚያሰሯቸው መስጊዶች የተለዩ ናቸው፡፡ እነዚህን በመድረሳ ትምህርት ቤትነት ገና በእውቀት ያልገፉ ወጣት ሙስሊሞችን በማስተማር የዋሀቢ አክራሪ እሥልምናን እንዲያስፋፉ የሚጠቀሙባት ነው፡፡

የዋሀቢ እሥላሚዊ አክራሪ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፡ በኢትዮጵያ የሚያካሂዱትን የዘመቻ ሥራ ለመደገፍ ገንዘብ እንዴት እንደሚያስገቡ የሚገልፀው የአሜሪካን ኤምባሲ መረጃ እጅግ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው በሣውዲ ዐረቢያና በገልፍ አገሮች በቤት ሠራተኛነት፣ በጉልበት ሠራተኛነትና በሌሎችም ሙያ በሚጠይቁ ሙስኮች ተሰማርተው የሚሰሩ እንዲሁም ከፍተኛ ክፍያ ያላቸውን ኢትዮጵያውያንን ጨምሮ የተለያዩ እቃዎችን በገንዘብ እንዲገዙ ከተደረገ በኋላ እነዚህ እቃዎች በድብቅ በሶማሊያና ጅቡቲ በኩል አድርገው ወደ ኢትዮጵያ እንዲገቡ ይደረጋል፡፡

ያለምንም ታክስ ግልፅ ገበያ ላይ እንዲሸጡ ተደርጎ (ከገበያ ዋጋ በታች) ከትርፉ ጋር ለዋሀቢ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ይሰጣል፡፡ በዚህ ገንዘብም የፈለጉትን ሥራ ከውኑበታል፡፡ በራሳቸው አምሳል በሚሰሩዋቸው አረንጓዴ ክብ መስጊዶች ከየአካባቢው ነዋሪ በተለይ በቀለም ያልገፉ ወጣቶችን በመመልመል መስጊዶቹን የመድረሳ ትምህርት ቤቶች በማድረግ አክራሪ እሥልምናን ማስፋፊያ ማዕከል በማድረግ ይጠቀሙበታል፡፡

በዚህ መልኩ ለበጎ አድራጎትና የቲም (የሙት) ልጆችን ለመርዳት በሚል ከኢትዮጵያ መንግሥት የሥራ ፈቃድ አግኝተው በአዲስ አበባና በክልሎች ሲንቀሳቀሱ የነበሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ እሥላሚዊ ድርጅቶች በተለይም የሠውዲ ዐረቢያ፡ የኳታርና የኩዌት የዋሀቢ አክራሪ እሥልምናን እምነት ለማስፋፋት ድምፃቸውን አጥፍተው ሲሰሩ የኖሩ ቢሆንም የዘያኑም ያህል መንግሥት ክትትል እያደረገ ከአገር ለቀው እንዲወጡ አድርጓል፡፡

ከዚህም ሌላ በአገር ውስጥ በሙስሊም መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ለሙሥሊም የደሀና የሙት ልጆችን ለመርዳት በሚል የተቋቋሙ በዋናነት የገንዘብ ምንጫቸው ሣውዲ ዐረቢያና ሌሎች የዐረብ አገራት ናቸው፡፡ ከ200 - 300 በመኖሪያ አድራሻቸው በትምህርት ደረጃቸው የሚመዘገቡት ሕፃናት ሙሊሞች ፎቷቸው ጭምር እንዲላክ ተደርጎ ገንዘቡ በድርጅቱ አድራሻ በተለያየ ማገድና ዘዴ እንዲገባ ይደረጋል፡፡

ለአንድ ተረጂ ልጅ መቶ ዶላር እንደሚላክ የሚገልፁ ወስጥ አዋቂዎች ለልጆቹ ቤተሰቦች ግን የኢትዮጵያ 200 - 300 ብር ብቻ እያስፈረሙ እንደሚሰጡ ያስረዳሉ፡፡ ዋናው ጥያቄ ቀሪውና ዋናው ገንዘብ የት ይሄዳል? ለምንስ ዓላማ ይውላል? የሚለው ነው፡፡

የተወሰኑት ለግል ማከበሪያቸው ሲያደርጉት ሌሎች ደግሞ ቀድሞም በሸፋን ለተቋቋሙት አክራሪ እሥልምና ኃይሞኞትን ለማስፋፋት ወደ ዋሀቢዎች የገንዘብ ቋት እንደሚገባ ማጠራጠር አይቻልም፡፡ በዚህም ሚልኩ ሲንቀሳቀሱበት ኖረዋል፡፡

የዋሀቢ አክራሪ እሥልምና እምነት አራማጆች በተለይ ሙሉ ትኩረት ያደረጉት ወጣቱ ሙሥሊም ላይ ነው፡፡ ይኸ ኃይል በእነሱ ፅንፈኛ እምነትና ፕሮፓጋንዳ ከተቀረፀና ከተሙሉ በየደረጃወም በከፍተኛ ገንዘብ ከታገዘ፣ በሸፋን የራሱን የንግድ ድርጅት አቋቁሞ በተለያዩ የንግድ ማስኮች ሥራ ገንዘብ ተሰጥቶት እንዲንቀሳቀስ ከተደረገ፡ ዓላማውንና መዋቅሩን ለማስፋፋት ከተጋ ወጤታማ ነው ብለው ያምናሉ፡፡ በዚህ ሚልኩ ለረዥም ገዜ ኢትዮጵያ ወስጥ ከከተማ እስከ ገጠር ሲሰሩ የኖሩት ወጣት ሙሥሊሞችን በአክራሪ የዋሀቢ እሥልምና እምነት የማጥመቅና የማዘጋጀት ሥራ ነው፡፡

የዋሀቢ አክራሪዎች የሱፊ እሥላም ኢትዮጵያዊ መሠረት ያለውን የአልሀበሽ እሥልምና እምነት አምርረው ይጠሉታል፡፡ ይዋጉታልም፡፡ ዋሀቢዎች በአማራውና በኦሮሚያ ክልሎች መንግሥታዊ ባልሆኑ እሥላማዊ ድርጅቶች ከፍተኛ ገንዘብ እየታገዙ ወጣቱን እየማለሙ ዓላማቸውን በስፋት በሕዝበ ሙስሊሙ ወስጥ ለሚድረስና ሙሉ በሙሉ ለማለወጥ ቢንቀሳቀሱም አልተሳካላቸውም፡፡ በአፀፋው ከፍተኛ ተቃውሞና ውግዘት ደርሶባቸዋል፡፡

ዋሀቢዎች የነቢዩ ሙሀመድ መውሊድ (የተወለዱበት ቀን) ማከበር የለበትም፡ እነሱ ከሚያሰሩት መድረሳቸው፡ ከሚያስተምሩበት ማስጊድ ውጭ ሌላ የሙሥሊሞቸ ማስጊድ መኖር የለበትም ይላሉ፡፡ ወልየችና ታላላቅ የሱፊ እሥላም ሼሆች ቢያልፉም ሕዝቡ የሚያምንባቸውን መቃብራቸውን ቆፍሮ በማውጣት እንዲቃጠል አድርገዋል፡፡

የተለያዩ የሱፊ እሥልምና ተከታዮች የእምነት ሚራመጃ ማስጊዶችንም አቃጥለዋል፡፡ በባሌ ሼክ ሁሴን በብዙ መቶ ሺህ የሚቆጠር ሕዝብ በተለያየ ጊዜና በየዓመቱ ከተለያየ ክፍለ ሀገር እየሄደ የሚዘይርበትን፡

እምነቱን በነፃነት በሚያራምድበት ሥፍራ ከ30 በላይ መስጊዶችን አቃጥለዋል፡፡ ሕዝበ ሙስሊሙም በከፍተኛ ተቃውሞ አውግዟቸዋል፡፡

በድሬዳዋም የአባድር መስጊድንና የተለያዩ ሼሆች መቃብሮችን እየቆፈሩ በማውጣት ለማቃጠል ያደረጉት ሙከራ በሕዝበ ሙስሊሙ ጠንካራ ትግል ከሽፏል፡፡

በወሎ ከ1 ሺህ 720 አካባቢ ጀምሮ ንጉሥ መጃሂዱ የመሠረቱትና በየዓመቱ የነቢዩ መውሊድ የሚከበርበትን ታሪካዊውን የጃማ ንጉሥ መሥጊድ በየዓመቱ ለበዓሉ ለሦስት ተከታታይ ቀናት ከወሎ ብቻ ሳይሆን ከተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች በመጓዝ ከመቶ ሺህ በላይ ሙስሊሞች ያከብሩታል፡፡

ይህ መስጊድ ከ240 ዓመት እድሜ በላይ ያስቆጠረ ጥንታዊ ቅርስ ነው፡፡ በአካባቢው የነበረው የኩዌት መንግሥታዊ ያልሆነ እሥላማዊ ድርጅት መስጊዱን ለማደስ እርዳታ እንዲያደርግ ቢጠየቅ ከልክሏል፡፡

የሣዑዲ ዐረቢያና የኳታር ኤምባሲዎችም ቢጠየቁ እርዳታ ከልክለዋል፡፡ እነሱ የሚፈልጉት እንዲጠፉ እንጂ ቅርስነቱ ተጠብቆ የእምነቱ ቦታ ተከበሮ እንዲኖር አይደለም፡፡ በዚህ መሃከሉ ከታሪካዊ ቅርስነቱ አንፃር መስጊዱን ለማደስ ጥያቄ የቀረበለት የአሜሪካ ኤምባሲ እገዛ አድርጓል፡፡

ወሎ ከጥንት ጀምሮ ስማቸው ገኖ የተጠራ የሙሥሊም ወልዮችና ሼሆች የነበሩባትና ያሉባት ነች፡፡ እነ ሼህ ሁሴን፡ እነ ቦረናው ሼህዬ፣ እነ ሰይድ ቡሽራ፡ የሚሣው ሼህዬን እስከ ዛሬም ድረስ ሕዝቡ በእምነቱ የሚከርፍባቸውን ጥንታዊ መስጊዶች ከብዙው በጥቂቱ ማንሳት ይቻላል፡፡

ተመሣሣይ መስጊዶች በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ይገኛሉ፡፡ ኢትዮጵያዊ ታሪክና አሻራቸው የገዘፈ ነው፡፡ ዋህቢዎች እነዚህ ሁሉ መጥፋት አለባቸው ብለው ነው ዘመቻ የከፈቱት፡፡ በርካታ አዛውንት የሱፊ ሙሥሊም ሼሆች በተለያዩ ሥፍራዎች በዋሀቢ አክራሪዎች ተዘልፈዋል፡፡ ተሰድበዋል፡፡ ተደብድበዋል፡፡ ተገድለዋል፡፡ መስጊዳቸውም ተቃጥሏል፡፡

ይኸ እውነት ጊዜውን ጠብቆ አሁን በአደባባይ ታወቋል፡፡ ሁሉም ሙሥሊም የአክራሪዎቹን ማንነትና ምንነት ለይቶ አውቆታል፡፡ መነሻውን ሣውዲ ዐረቢያ ያደረገው የዋሀቢ አክራሪ እሥልምና እምነት ጥንታዊ መሠረት ያለውን የኢትዮጵያ እሥልምና በማፍናቅ የእኛ ብቻ ነው ትክክል ይላል፡፡

የእኛዎቹ የገንዘብ አቅም ስለሌላቸው ዋሀቢዎች በገንዘብ ኃይል የኢትዮጵያ ሙሊምን ታሪክና አሻራ ለማጥፋት መፅሀፍቶችን አቃጥለዋል:: በኢትዮጵያ የተከሰተው አክራሪ የዋሀቢ እምነት አራማጅና የንቅናቄው መሪዎች በሙሊሙ ወስጥ የተለያዩ ያዋጣናል ያሉትን መንገዶች ሁሉም ተጠቅመዋል::

ቀድሞ በ1993 በኢትዮጵያ የእሥልምና ጉዳዮች ምክር ቤት ከፍተኛ አለመግባባት ሲከሰት፤ ከዚያም በኋላ ንብረት የወደመበት፡ የሰው ሕይወት ያለፈበትና ሁኔታው በቁጥጥር ስር ወሎ ወደ ፍርድ ቤት ከሄደበት ታሪክ ጀርባ እንዲህ እንደ አሁኑ ለይቶና አፍጥጦ ባይወጣም የዋሀቢ እሥልምና አክራሪዎች እጅ በዋናነት ነበረበት::

ለዚህ ማስረጃው ዊክሊክስ በአዲስ አበባ የአሜሪካን ኤምባሲ ወደ ዋሽንግተን የላከውን ሚሪጃ ሲያወጣ ዋሀቢዎች የኢትዮጵያ እሥልምና ከፍተኛ ጉባዔን አሚራር በእኛ ብቻ የሚሚራ፡ በእኛም አምሳል የሚቢጠር መሆን አለበት የሚል ድርጅታዊ ውሣኔ አሳልፈው በአባሎቻቸውና በተባባሪዎቻቸው አማካይነት ሲንቀሳቀሱ መቆየታቸውንና በማንቀሳቀስም ላይ እንዳሉ ይፋ አርደጓል::

ስለዚህም በሙስሊሙ ኅብረተሰብ ወስጥና በሞርካቶ አንዋር መስጊድ የፈጠሩት መሻሻውን አስተዳደራዊ ጥያቄ ያደረገው እንቅስቃሴ የላይኛውና ከውጭ የሚታየው ሽፋን ነው:: ይኸን ችግር ለመፍታት መንግሥት የበኩሉን ከፍተኛ ጥረት አድርጓል::

እንቅስቃሴው ግን ቀድሞ የታቀደበት ግብ ስለነበረ ወረቀት ማብተን፤ በሌሊት የመስጊድ የአደጋ ጥሪ መደወልና በኢሜል በሚዲያና በተላላኪ በመላው አዲስ አበባ ቅርብ ከተሞች እንዲሁም በክፍላተ አገራት በተመሣሣይ ሰዓት ሕዝበ ሙስሊሙ ግልብጥ ብሎ እንዲወጣ ክርስቲያኑም እንዲተባበር ለማድረግ ትልቅ ጥረት አድርገዋል:: አልተሳካላቸውም::

ታዲያ ይኼ እንዴት በመስጊድ አሚራር፣ በአወሊያ ትምህርት ቤት ጉዳይ የተነሳ የአስተዳደር ጥያቄ ብቻ ነው ተብሎ ይወሰዳል? በነገራችን ላይ የአልቃይዳ እሥላሚዊ አክራሪና ዓለም አቀፍ አሸባሪ የድርጅቱ ሙሥራችና መሪ የነበረው ቢንላደን የዋሀቢ አክራሪ እሥልምና አራማጅ ነው::

በዚህ ጥቂት ዋሀቢዎች በፈጠሩትና ወደ አብዛኛው ሕዝበ ሙስሊም በአስተዳደር ጥያቄ ስምና ሽፋን ፓለቲካዊ አጀንዳቸውን ለሚራመድ ሲንቀሳቀሱ ግባቸው በኢትዮጵያ በሸሪዓ ሕግ የሚሚራ እሥላሚዊ መንግሥት መሙሰረት ስለመሆኑ ሌላም ማስረጃ አለ::

ኢትዮጵያወያን የሱፊ ሙስሊም ተከታይ የሆኑ ዑላሞችና ሼሆች ልጆቻቸውን ደጋግመው ለማካር እንደሞከሩ ተናግረዋል፡፡ በእምቢተኝነት እስከ ግድያና የኃይል እርምጃ ድረስ እንደተራመዱም አባቶች ያስረዳሉ፡፡

ከሣዑዲ ዐረቢያ ተቀርፆ ወደ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ የገባወና በሙስሊሙ ወስጥ በህገ ወጥነት የተሰራጨው የቅስቀሳ ሲዲ ''ወደዱም ጠሉ አገሪቷ (ኢትዮጵያን) የካፊሮች ነች የሚሉት ተሳስተዋል፡፡ አገሪቷ የማንም ሳትሆን የእኛ ነች፡፡ ለሌሎች የሞራል መብት እንኳን አንሰጣቸውም፡፡ እንቅስቃሴወን ጀምረናል፡፡ አላህ ይረዳናል፡፡ ወደ ኋላ መማለስ የለብንም ሲል ኢትዮጵያዊው የዋሀቢ ሚሴ ተናግሯል፡፡

ሌላዋ ሴት ደግሞ ጅሀድ አወጀውብናል፡፡ እኛም መነሳት አለብን'' ብላለች፡፡ ይኸው በምስጢር በብዛት የተሰራጨው ሲዲ የዋሀቢው ሚሴ ንግግር ሲያደርግ አብሮ የሚታየው የጅሀድ አክራሪ ተዋጊዎች የተለያዩ ወታደራዊ ሥልጠናዎች ናቸው፡፡ መሣሪያ ታጥቀው ሲንቀሳቀሱ በሀገድ ያሳያል፡፡

እጅጉን በሚገርም ሁኔታ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፓለቲካ ፓርቲዎች ይህንን በኢትዮጵያ ላይ የታወጀ የጅሀድ ጦርነትን የአስተዳደር ጥያቄ ነው፡ መንግሥት ጣልቃ ገብቷል የሚሉት፡፡

ነገ እነሱስ ወደ ሥልጣን ቢመጡ ኢትዮጵያ በዋሀቢ ጅሀዲስቶችና አክራሪ ሙስሊሞች ተወርራ እንድትጠፉ ይፈቅዳሉ ማለት ነው፤ የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው የሚለውን ከሠይጣንም ጋር ቢሆን ተባብረን ኢሕአዴግን ከሥልጣን እናስወግዳለን የሚል ጅል ሚኪር ይዘዋል፡፡

እንዲህ ዓይነቱ የፓለቲካ ብስለት ወይንም ስትራቴጂ ነው ብለው አስበውት ከሆነ ደግመው ራሳቸውን ይመርምሩ፡፡ ይህ ብስለት ሳይሆን አሳፋሪ የፓለቲካ ዝቅጠት ነው፡፡ እናስብለታለን የተሻለ እንመራታለን፣ ታሪኳንና ክብሯን እንጠብቃለን በሚሏት ኢትዮጵያ ላይ የጅሀድ ጦርነት ሲታወጅ አብሮ ማስለፍ ታላቅ የአገር ክህደት ነው፡፡

የዋሀቢ አክራሪ ሚሴ በወታደራዊ ሥልጠና የመሣሪያ ትጥቅ በታጀበ፡ የጠራ አማርኛ እየተናገረ ወደ ኢትዮጵያ በላከው የሲዲ ሚልዕክት፣ ''ይህች አገር የእኛ ናት! የካፊሮች አይደለችም፡ ከተፈለገም ስሟን ተስማምተን እንቀይራለን!'' ይላል፡፡ ኢትዮጵያ የሚለው ስም እንዲቀየር ማለት ነው፡፡ ይህንንስ ያፈጠጠ ያገጠጠ እወነት ኢሕአዴግ ያዘጋጀው ፕሮፓጋንዳ ነው በማለት ዛሬም ራሳችሁን ታታልሉትና ታፅናኑት ይሆን? ይህ አፍጥጦ የመጣ የአክራሪነት አደጋ ለተቃዋሚውም ለሕዝቡም ብሎም ለአገሪቱ ትልቅ አደጋ ነው፡፡ ችግሩ የመንግሥት ብቻ አይደለም፡፡

ተቃዋሚው ከኢሕአዴግ ጋር የቱንም ያህል የፓለቲካና የሚስጥ ልዩነት ቢኖረውም ፅንፈኛና አክራሪ ከሆነ፡ የኢትዮጵያን ጥንታዊ ታሪክ፡ የሙስሊሞችን ታሪክና እምነት ማስጊድ ጭምር ለማጥፋት ወስኖ ከሚንቀሳቀስ ኃይል ጋር የአስተዳደራዊ ጥያቄ ነው፤ አክራሪነት በኢትዮጵያ የለም ብሎ መግለፅና አብሮ መቆም፣ ድጋፍን ማስጠት፤ በታሪክም በትውልድም ፊት አሳፈሪና አሳዛኝ ተግባር ነው፡፡ ለዚያውም ተቃዋሚው ራሱ ይደግፈኛል ብሎ ከሚለው ከአሜሪካ መንግሥታዊ ተቋም የተገኘው ግልፅና ተጨባጭ ማስረጃ እያለ፡፡

የዋህቢ አክራሪ እሥልምና እምነትን በኢትዮጵያ ለማስፋፋት ወስጥ ለወስጥ ለበርካታ ዓመታት መዋቅር ዘርግቶ ሲንቀሳቀስ፡ አባላት ሲያፈራ፡ ሲያሰለጥን፡ ሲያደራጅ የኖረው ድርጅት ከዋራጃ የተባለ ወታደራዊ ክንፍም አለው፡፡ ይኸው ወታደራዊ ክንፍ በመንግሥት እርምጃ ተወስዶበት ቀንደኛ መሪዎቹና ኃይሉ ተመትቷል፡፡

ወታደራዊ ክንፉ ሼሆችን ገድሏል፣ አልፎም ቤተክርስቲያንና ማስጊዶችን አቃጥሏል፡፡ አባቶችና እናቶች ተገድለዋል፡፡ ለጊዜውም ቢሆን የወታደራዊ ክንፉ እንቅስቃሴ በተወሰደው እርምጃ የተገታ ቢሆንም ከኃይል መድከምና አቅም ማጣት ካልሆነ በስተቀር ተመልሶ አይከሰትም ማለት አይቻልም፡፡

በኢትዮጵያ የዋህቢ እሥላማዊ አክራሪነት መከሰቱና የቻለውን ያህል በተለያየ ሽፋን አድብቶ ለማስራፋት ማጣከሩ በገሀድ የታየና የተረጋገጠ እውነታ ነው፡፡ ይህን አደጋ መካላከል የሁሉም ዜጋ የሕልወናም የሠላምም ወሣኝ ጥያቄ ነው፡፡